# ከኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡
# ለአቶ ራፋቱኤል ደስታ ወርቁ ሒስ
## የተሰጠ መልስ።

አቶ ራፋቱኤል! ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥትን፡ እስካኹን አላወቋትምን? አያምኑባትምን? ልጇና ነጋሢዋ፥ ካህኗና ዜጋዋ መኾንን መምረጥ አልፈለጉምን? የራሷ ፃማ ሀብቷ የኾነው፡ "ተዋሕዶነት" እንጂ፡ የኋለኛነትና የተከታይነት፥ የቅኝ ተገዢነትና የኑፋቄ መታወቂያና ማረጋገጫ ምልክት የኾነው "ኦርቶዶክስነት"፡ ለእርሷ፡ ምኗም እንዳልኾነ፡ እስከዛሬ አልተገነዘቡምን?

በቅድሚያ፡ ለእነዚህ ጥያቄዎች፡ መልስ ሊሰጡ ይገባል። መልስዎ፡ በሙሉ፡ አዎንታዊ በኾነ ኖሮ፡ ገንቢ ውይይታችንን በቀጠልን ነበር፤ ነገር ግን፡ እንዲህ ስላልኾነ፡ እርስዎንና እኛን የሚያገናኘንና የሚያነጋግረን፡ አንዳችም ምክንያት ስለሌለ፡ የአሳብ ልውውጣችንን፡ እዚሁ ላይ ማቆም ግድ ይኾንብናል።

ይኹን እንጂ፡ የበጎ አስተዋዮችና የቅን አንባቢዎቻችን፡ የእውቀት አድማስ ይሰፋ ዘንድ፡ እርስዎ በሠነዘሯቸው የሒስ አስተያየቶችዎ ውስጥ፡ ላወሷቸው የትችት ነጥቦች፡ የምናብራራው ቍም ነገር ስላገኘንበት፡ ያንን፡ ከዚህ እንደሚከተለው ባጭር አቅርበናል።

፩ኛ፡ ለመኾኑ፡ ወላጅ አባትዎ፡ ምን ያህል የሚወድዱዎና ራስዎን፡ ለታላቅ ቍም ነገር እንዲያበቁላቸው፡ የቱን ያህል የሚጥሩልዎ፡ እውነተኛ የእግዚአብሔር ሰው፥ እውነተኛ ኢትዮጵያዊ ቢኾኑ ነው፡ ለ፲፰ኛው ዓመት የልደት በዓልዎ፡ ልዩ ማስታወሻና ብርቅ መታሰቢያ እንዲኾንዎ፡ በዓለማዊ ዋጋውም ኾነ ጠቃሚነቱ፣ ቋሚ ቅርስነቱም ኾነ ሀብትነቱ፡ የበለጠ ክብርና ደረጃ ያለውን፡ ሌላውን፡ የስጦታ ዓይነት ኹሉ ትተው፡ ከዚያ ይልቅ፡ አነስተኛ መስላ የምትታይ፥ ገበታዋ እንኳ፡ በኹለቱም ፊት፡ ሌጣ ኾኖ፡ ምንም ዓይነት ማራኪ ሥዕል የሌላትን፡ "ኢትዮጵያዊው፡ በማንነቱ ፍለጋ!" የምትለውን መጽሓፍ መርጠው፡ ሊያበረክቱዎ የፈለጉት? አባትዎ፡ ይህን ያደረጉት ለምን መስሎዎ ኖርዋል?

በእርስዎም በኩል፡ መጽሓፊቱን ብቻ ሳይኾን፥ ደራሲዋን ጭምር፡ በጣም እንደወደዷቸውና እንዳከበሯቸው ተናግረዋል? ለምን? አባትዎ፡ የልደት ቀንዎ ሽልማት አድርገው ስለሰጡዎ ነውን? ወይስ፡ የመጽሓፊቱን መልእክት አምነውበት ስለተቀበሉት ነበር? እውነታው፡ ይህኛው ከኾነ፥ ማለትም፡ ለደራሲውም ኾነ፥ ለድርሰቲቱ፥ ለኹለቱም፡ ያን የመሰለ ፍቅርና ክብር ያሳዩት፡ መልእክቱ፡ በትክክልና በእርግጥ ገብቶዎት ከኾነ፡ ታዲያ አኹን ለምን፡ ያን፡ የፍቅርና የክብር ግምትዎን የሚለውጥ ኹኔታን ሊያሳዩ በቁ?

አዩ! የመጽሓፉ መልእክት፡ ፈጽሞ ያልገባዎ፥ ፈጽመው ያልተረዱትም መኾንዎን፡ ይኸው፡ በአኹኑ አገላለጽዎ አረጋግጠው አሳይተዋል። ስለኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት የተሰጠው፡ የአርባ ዓመታቱ አስተምህሮ ውጤት፡ እንግዴህ፡ ይህ፡ በእርስዎ የተነገረውና በእርስዎ ላይ የታየው ኹኔታ ነው። እርስዎና እርስዎን የመሰሉት ወጣቶች፡ ጥንታዊና ቀዳማዊ፥ መሠረታዊና ፍጹማዊ፥ አማናዊና መለኮታዊ የኾነውን፡ ኢትዮጵያዊ ማንነታችሁን፡ አጥርታችሁና አስተካክላችሁ እንድታውቁ፥ አውቃችሁም፡ የኢትዮጵያ የኾነውን ኹሉ፡ ለይታችሁና አጽንታችሁ እንድትይዙት፥ እንድትጠቀሙበትም እንጂ፡ ያን ትታችሁ፥ ይባስም ብላችሁ፡ እርሱን እየተቃወማችሁ፡ እርሱን ለማጥፋትና ለመደምሰስ፡ ለሦስት ሽህና ለአንድ ሽህ ስድስት መቶ ዓመታት፡ ሲጥሩ ለኖሩት፡ ለኦሪታውያኑ አይሁድና ለኦርቶዶክሳውያኑ ግብፆች ባሮችና ተገዢዎች ኾናችሁ፡ ለእነርሱና የእነርሱ ቅርስ ለኾኑት የሰውኛ ሥ'ርዓቶቻቸው፡ አገልጋዮችና አፈ ቀላጤዎች እንድትኾኑ አልነበረም።

ለእኒሁ ኦሪታውያን አይሁድ መሣሪያ ኾኖ፡ ዓላማቸውን ሲያራምድ ከሚታየው፡ "ማኅበረ ሥላሴ ዘደቂቀ ኤልያስ" ከተባለው ስብስብ ቀርቶ፥ ለኦርቶዶክሳውያኑ ግብፃውያን፡ በኢትዮጵያ፡ ቅርንጫፋቸው ኾና ከምታገለግላቸው፡ ራስዋን፡ "የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን" ብላ ከምትጠራውና ቅዱሱን ኪዳን፡ በምሥጢር ብቻ ሳይኾን፡ በይፋ ከካደችው፥ በቸሩ ፈጣሪና በቅድስት እናቱ ላይ ካመፀችው፥ በአምልኮ አመንዝራነት አበሳም ከተጨማለቀችው፥ ከዚህ ኹሉ ኃጢኣቷ የተነሣም፡ በመለኮት ውግዘት ውስጥ ከምትገኘው፡ የክፉዎች ድርጅት ጋር እንኳ፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ እንዴትና ምን ተካፋይነት፥ ምን ኅብረትና መስማማት፥ ምን ክፍልና መጋጠም ይኖራታል? ጨርሶ ሊኖ ራት አይችልም።

ጀግናውና ታማኙ ኢትዮጵያዊ ሓዋርያ፡ ቅዱስ ጳውሎስ፡ ለእውነተኞች ምእመናንና ምእመናት ተከታዮቹ፡ እንዲህ ሲል እንደጻፈው። "ኢትኩኑ ንፉቃነ! ወኢትሑሩ ውስተ አርዑተ፡ እለ ኢየአምኑ!"

ማለትም፡ "ተጠራጣሪዎች አትኹኑ! በማያምኑ ወገኖች ቀንበርም እንዳትጠመዱ፡ ወደእነርሱ ጉባኤ አትኺዱ!" ብሎ ካስጠነቀቃቸው በኋላ፡

"መኑ፡ ዘያስተዔርያ ለጽድቅ፡ ምስለ ኃጢኣት? ወመኑ፡ ዘይዴምሮ ለብርሃን፡ ምስለ ጽልመት? ወመኑ፡ ዘየኅብሮ ለክርስቶስ፡ ምስለ ቤልሆር? ወመኑ፡ ዘይከፍሎሙ ለመሃይምናን፡ ምስለ ንፉቃን? ወመኑ፡ ዘይዴምር ታቦተ እግዚአብሔር፡ ውስተ ቤተ ጣዖት? አኮኑ ንሕነ ውእቱ፡ ቤቱ ለእግዚአብሔር ሕያው፡ በከመ ይቤ እግዚአብሔር፡ ‹አነ አኀድር ኀቤሆሙ፤ ወአንሶሱ ማእከሎሙ፤ ወእከውኖሙ አምላኮሙ፤ ወእሙንቱኒ፡ ይከውኑኒ ሕዝብየ! ወበእንተ ዝንቱ፡ ፃኡ እማእከሎሙ፤ ወተፈለጡ እምኔሆሙ!› ይቤ እግዚአብሔር፤ ‹ወኢትቅረቡ ኀበ ርኩሳን፤ ወአነ እትዌከፈክሙ፤ ወእከውነክሙ አባክሙ! ወአንትሙኒ ትከውኑኒ ደቂቅየ፥ ወአዋልድየ!› ይቤ እግዚአብሔር፡ ዘኵሎ ይመልክ።"

ማለትም፡ "እውነትን፡ ከሓሰት ጋር፡ የሚያስተካክላት፡ ማነው? ብርሃንንስ፡ ከጨለማ ጋር የሚቀላቅለው ማነው? ክርስቶስን፡ ከሰይጣን ጋር የሚያስተባብረው፡ ማነው? የእግዚአብሔር አማኞችንስ፡ ከተጠራጣሪዎች ጋር አንድ ወገን የሚያደርጋቸው ማነው? የእግዚአብሔርን ታቦትስ፡ በጣዖት ቤት ውስጥ የሚያኖር ማነው? የሕያው እግዚአብሔር ማደሪያዎች፡ እኛ አይደለንምን? እግዚአብሔር እንዳለ፡ ‹እኔ፡ በእነርሱ አድራለሁ፤ በመካከላቸውም እመላለሳለሁ፤ አምላካቸውም እኾናቸዋለሁ፤ እነርሱም፡ ሕዝቤ ይኾኑኛል። ስለዚህም፡ ከመካከላቸው ተለይታችሁ ውጡ! ከእነርሱም ተለዩ!› አለ እግዚአብሔር፤ ‹ወደርኩሳንም አትቅረቡ! እኔም፡ እቀበላችኋለሁ። አባት እኾናችኋለሁ፤ እናንተም፡ ወንዶችና ሴቶች ልጆች ትኾኑኛላችሁ።› አለ፡ ኹሉን የሚገዛ እግዚአብሔር።" (፪ቆሮ. ፮፥ ፲፬-፲፰።)

ስለዚህ፡ እርስዎና እርስዎን የመሰሉት ወገኖች፡ አማናዊቷ ኢትዮጵያ አገራችንና ሃይማኖታችን፥ እናታችንና ንግሥታችን ከኾነችው፡ ከቅድስት ድንግል ማርያምና ከኢትዮጵያዊ ልጇ፡ ከፈጣሪያችንና መድኃኒታችን፥ ሊቀ ካህናታንና ንጉሠ ነገሥታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይልቅ፥ እነርሱም ከሚመሯት፡ ከኢትዮጵያ የእግዚአብሔር መንግሥታቸው ይልቅ፡ አኹንም፡ የምንወድደውና የምንመርጠው፥ የምንከተለውና የምናገለግለው፡ እነዚያዎቹ፡ ኦሪታውያኑ አይሁድና ኦርቶዶክሳውያኑ ግብፃውያን፡ "መሥርተናታል! አቋቁመናታል!" ብለው፡ በቅኝ ገዥነት ሲመሯትና በማናለብኝነት ሲመዘብሯት የኖሩትን፥ ራሷንም፡ "የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን" ብላ የምትጠራውን፡ የዛሬዪቱንና ዘመናዪቱን፡ ከዳተኛዪቱንና ዐመፀኛዪቱን፥ አመንዝራዪቱንና ጥፉዪቱን ቤተ ክህነት ነው!" ማለታችሁ፡ በምንም መልኩ፡ ከቶ አያስደንቅም።

ከዚህ የተነሣ፡ ጥላቻችሁና ጠባችሁ፥ ተቃውሟችሁና አሳዳጅነታችሁ፡ በመጽሓፊቱ ደራሲ ላይ አይደለም፤ እርሱማ፡ ምንድር ነው? ኢምንት አይደለምን? ከምንስ የሚቆጠር ነው? አንድ ምስኪን፡ አይደለምን? እርሱን፡ ጠላችሁትና፡ ምን ይጎዳችኋል? ወደዳጅሁትናስ፡ ምን ይጠቅማችኋል?

ጥላቻችሁና ጠባችሁ፥ ተቃውሟችሁና አሳዳጅነታችሁ፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ላይ መኾኑን፡ እርስዎና መሰሎችዎ በእርግጥ አውቃችሁታል። ታዲያ! ካወቃችሁት፡ አጻፋውን መቋቋም፡ ለእናንተ ይቻላችኋልን? ይበጃችኋልስ? አትችሉትምና፡ ለተቃዋሚው ኦሪታዊ፡ "ይብእሰከ ረጊጽ፡ ውስተ ቀኖት በሊህ!" ማለትም፡ "የጦሩን ስለት ብትረግጥ፡ ጉዳቱ፡ ለአንተው ይብስብሃል!" ያለው፡ መለኮታዊ ማስጠንቀቂያ፡ ሳውልን፡ ወደጽድቅ እንደመለሰውና ለፍቱን መሣሪያነት እንዳበቃው ኹሉ፡ እናንተም፡ በንስሓ ተመልሳችሁ፡ እየራሳችሁን፡ ለኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ልጅነትና ነጋሢነት፥ ካህንነትና ዜግነት ብታበቁ ይሻላችኋል! (የሓዋ. ፱፥ ፭።)

፪ኛ፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ቀድሞም ኾነ ዛሬ፡ አጽንታ የቀጠለችው ሥርዓት፡ ያንኑ፡ ለ፯ሺ፭፻፮ (ለሰባት ሽህ አምስት መቶ ስድስት) ዓመታት፡ ሕያው ኾኖ የኖረውን፡ የፈጣሪዋን የእግዚአብሔርን መለኮታዊ ሥርዓት እንጂ፡ ሰይጣናዊና ሟች የኾነውን፡ የሰዎችን ሥርዓት አይደለም። ያም፡ የእግዚአብሔር ሥርዓት፡ በቅዱሱ ጋብቻ ላይ የተመሠረተው፡ ቤተሰባዊና ማኅበራዊ ኑሮ እንጂ፡ የዛሬ አንድ ሽህ ስድስት መቶ ዓመታት፡ በግብፃውያኑ ገዳማውያን ተውጥኖ የተመሠረተውን የምንኵስናና የገዳማዊ ኑሮን አይደለም።

የእግዚአብሔሩ የኾነውማ፡ መጀመሪያ፡ በአዳምና በሔዋን፥ ተያይዞም፡ በእነኄኖክና ቅድስት ብእሲቱ፥ በነኖኅና ኀይከል፥ እስከመልከጼዴቅና ሳሌም፥ ከዚያም፡ ከኢትዮጵያዊው ኢያቄምና ከኢትዮጵያዊቷ ሐና ደርሶ፥ እግዚአብሔር አብ፡ በእርሱ ሙሽርነትና በእርሷ ሙሽሪትነት፡ ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን በወለደችለት በኢትዮጵያዊቷ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ በዘለዓለማዊነት ያተመው፥ በመጨረሻም፡ በቃና ዘገሊላ የቀደሰውና ያጸደቀው ሥርዓተ ጋብቻ ነው።

እግዚአብሔር፡ ይህ ሥርዓቱ፡ በዚህ፡ በጋብቻ መልኩ ብቻ ሳይኾን፡ በሰብአዊው የጾታ ልዩነቱና የአካለ ሥጋ ብልቶቹ፥ በተፈጥሮአዊው ፍትወቱና የልደት ውበቱ ጭምር፡ አሳምሮና አስጊጦ ባስገኘው፡ የሥነ ፍጥረት ትንግርቱ፡ አግዝፎና ሕያው አድርጎ፡ ለፍጹምነትና ለዘለዓለማዊነት አብቅቶታል።

ለዚህም ማረጋገጫ፡ ሌላ ምስክርና ማስረጃ አያስፈልግም። በቅዱሱ ኪዳን ውስጥ የተጠቃለሉት፡ ሰባቱም የእግዚአብሔር ቃል ኪዳናት፡ የተደረጉት፡ ከድንግላውያን፥ ወይም፡ ከመነኰሳት ጋር ሳይኾን፡ ኹሉም፡ በጋብቻ ሥርዓት ተውስነው በሚኖሩ ሕጋውያን ባልና ሚስት አማካይነት መኾኑ ብቻ ይበቃል፤ ይኸውም፡ ፩ኛ. አዳምና ሔዋን፣ ፪ኛ. ኖኅና ኀይከል፥ ፫ኛ፡ መልከ ጼዴቅና ሳሌም፥ ፬ኛ. አብርሃምና ሣራ፣ ፭ኛ. ሙሴና ሲጳራ፥ ፮ኛ፣ ዳዊትና ቤትሳባ፣ በመጨረሻም፡ እግዚአብሔር አብና ቅድስት ድንግል ማርያም መኾናቸው ነው።

ራሱ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ለሐዋርያነት የጠራቸውና የመረጣቸው፥ በተለይም፡ ለሊቀ ሐዋርያነት የሠየመው ቅዱስ ጴጥሮስ ጭምር፡ ኹሉም፡ በቤተሰባዊ ሕይወት ይኖሩና ይዘጋጁ የነበሩ እንጂ፡ አንድም ገዳማዊ መነኵስ፡ በመካከላቸው ያለ አልነበረም፤ ለነገሩ፡ በዚያን ጊዜ፡ የምንኵስናው ወግ፡ ደብዛውም አልነበረም፤ ከ፬ መቶ ዓመታት በኋላ፤፡ በግብፅ በረሃ ብቅ እስኪል ድረስ።

በኢትዮጵያውያንና በኢትዮጵያውያት ዘንድ፡ የነበረው እጅግ ጥንታዊው የብሕትውናና የድንግልና አኗኗር ሥርዓት፡ ከዚህ፡ ከግብፃውያኑ የምንኵስናና የገዳማዊነት ኑሮ፡ እጅግ ይቀደመና የተለየ ሲኾን፥ ይኹን እንጂ፡ አሪታውያኑ አይሁድና ኦርቶዶክሳውያኑ ግብፃውያን መነኰሳት፡ ያን እግዚአብሔራዊዉን ኢትዮጵያዊ ሥርዓት አስወግደው፡ ይህን የራሳቸውን እስኪተኩ ድረስ፡ የኢትዮጵያ በኾነው ምድር ኹሉ ሠፍኖ ይሠራበት እንደነበረ፡ ግልጽ ነው።

ጥንታዊዉም ኢትዮጵያዊ የእግዚአብሔር ሥርዓት፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ "**አኮ፡ ለኵሉ ዘይትክሀል ዝንቱ፡ ዘእንበለ ለዘተውህቦ፤ እስመ ቦ ኅጽዋን፡ እለ ከማሁ ተወልዱ፡ እምከርሠ እሞሙ፤ ወቦ ኅጽዋን፡ እለ ኅጸውዎሙ ሰብእ፤ ወቦ ኅጽዋን፡ እለ ኅጸዉ ርእሶሙ፡ በእንተ መንግሥተ ሰማያት። ወዘሰ ይክል ተዐግሦ ለይትዐገሥ!**" ማለትም፡ "**ይህ፡ ለኹሉ የሚቻል አይደለም፤ ለተሰጠው ነው እንጂ። ከእናታቸው ማሕፀን፡ እንዲሁ የተወለዱ ዣንደረቦች አሉና፤ ሰዎች የሰለቧቸውም ዣንደረቦች አሉ፤ ስለመንግሥተ ሰማያት፡ ራሳቸውን ዣንደረባ ያደረጉ አሉ። መታገሥ የሚችልስ፡ ይታገሥ!**"" ብሎ፡ በአዲስ ኪዳኑ ዘመን የተናገረውን መለኮታዊ ቃሉን ተከትሎ ይፈጸም የነበረው ነው። ጌታችንም ይህን ቃል የተናገረው፡ ስለጋብቻና ስለትዳር ኑሮ፡ አይሁድ ፈሪሳውያን፡ በጠየቁት ጊዜ፡ ያለዝሙት ምክንያት፡ መፋታት እንደማይገባ ስለመለሰላቸው፡ "**የባልና የሚስት ሥርዓት፡ እንዲህ ከኾነ፡ ታዲያ! ማግባት፡ መልካም አይደለማ!**" ላሉት፡ ለደቀ መዛሙርቱ እንደነበረ ይታወሳል። (ማቴ. ፲፱፥ ፲፩-፲፪።)

እንግዴህ፡ ምንዥስና፡ ሰዎች የሠሩት እንጂ፡ የእግዚአብሔር አለመኾኑ፡ ከላይ ተመልክቷል። ከዚህ የተነሣ፡ እንዲያውም፡ እግዚአብሔር የሠራው፡ እጅግ ፍጹም መልካም የኾነው፡ የሥነ ተፈጥሮና የሥነ ህልውና ሥርዓት ጨርሶ የተቃወሰበት፡ የሰብአዊ ሕይወት ተጻራሪ ጠንቅ ነው፡ ሊባል ይቻላል፤ ምንዥስና።

ምንዥስና፡ እንዲህ፡ የእግዚአብሔርን የተፈጥሮ ሥርዓት የሚቃረንና የሚያቃውስ ከኾነ፡ ሓሳዊው መንፈስ ያሠረጸው መኾኑ፡ በግልጽ ይረጋገጣል። ይህም ኹኔታ፡ በኢትዮጵያ ሲካኼድ የኖረው፡ የእርስ በርስ እልቂት፡ ይደርስ የነበረው፥ ዛሬም እንኳ፡ በመካኼድ ላይ ያለውን፡ "አንተ ትነግሣለህ!" ወይም፡ "አንቺ ትነግሻለሽ!" ደግሞም፡ "'ወደፊት ይነሣል!' የሚባለው ቴዎድሮስ፡ አንተ ነህ!" እየተባለ፡ ለእርስ በርስ እልቂት፡ መነሻ የኾነው፡ የሓሣዊው መሢሕ፡ የንግርት ምንጭ፡ እኒሁ፡ "የበቁ አበው መነኰሳት ይገኙባቸዋል!" የሚባሉት ገዳማት አይደሉምን? የኣኹኑን፡ የዘመኑን ኢትዮጵያዊ ትውልድ፡ በሥጋዊው ፍትወታቸው ጽኑ ኃይል፡ እንዲህ የሚያምሱትና የሚያተረማምሱት፥ የሚያንከራትቱትና የሚያናውዙት፥ ያባዘኑትና ያባከኑት፥ ግራ የሚያጋቡትና ዕረፍት የነሡት፥ እርስ በርሱ የሚያጋጩትና የሚያናጩት፥ እንደመለኮታዊው የፍርድ ቃል፡ ለጥርስ ማፋጨትና ለልቅሶ ፍጻሜ የዳረጉት፡ በአገር ውስጥም ኾነ በውጭው ዓለም፡ የአሥረሽ-ምቺው ከተሞች መካከል ተንሠራፍተው የሚኖሩት፡ እኒህ ኹሉ መነኰሳትና ጳጳሳት፡ ከየት የተፈለፈሉ ናቸው? ከእነዚሁ፡ ከገዳማቱ አይደለምን?

እነዚሁ፡ የዛሬዪቱ ኢትዮጵያና ትውልዷ፡ ዕጣ ፋንታቸውና ዕድል ጽዋቸው፡ በአገር ውስጥም ኾነ፡ በውጭው ዓለም፡ እንዲህ፡ አስከፊና አሠቃቂ ኾኖ የቀረው፡ በእነማን መሠሪ ሥራ ነው? እነዚህ ገዳማት ባስገኟቸው፡ በእነዚሁ መነኮሳትና ጳጳሳት መኾኑን የሚያስተባብል፡ እውነተኛ ሰው ይኖራልን? ሊኖር አይችልም።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ "**ወእምፍሬሆሙ ተአምርዎሙ!**" ማለትም፡ "**ከፍሬአቸው ታውቋቸዋላችሁ!**" ሲል እንደተናገረው፡ መራራ ፍሬአቸውን፡ መላው ፍጥረተ ዓለም፡ በነቂስና በብርሃን ያለማቋረጥ የሚያየው አይደለምን? እነርሱስ፡ እግዚአብሔርን መፍራታቸው፡ ጥንቱንም ስለሌለ፡ ያ ቀርቶ፡ ያን የናቁትንና የሚያታልሉትን ሕዝብ እንኳ፡ ለእርሱ ጥቂት ይሉኝታ ኖሮአቸውና ኃፍረት ተሰምቷቸው፡ መርዛቸውን፡ በኅብረተ ሰቡ መካከል ከመርጨት ተግባራቸው በመከልከል፥ ያም ባይኾን፡ በመቆጠብ ፋንታ፡ እንዲያውም፡ በባሰ ይዞት፡ የጥፋት ተልእኳቸውን፡ ይኸው እንደቀጠሉበት አይደለምን? (ማቴ. ፯፥ ፲፮።)

በዚህ ረገድ፡ እጅግ አስገራሚና አሳዛኝ የኾነ፡ ሌላ የጥቃት ድርጊት አለ፤ ይኸውም፡ ጥንት፡ ከመጀመሪያው አንሥቶ፡ በኢትዮጵያውያንና በኢትዮጵያውያት ዘንድ ሲሠራበት የኖረውና የእግዚአብሔር የኾነው፡ ኢትዮጵያዊው የጋብቻና የትዳር ሥርዓት፡ ተንቆና ተዋርዶ፥ ተጥሎና ተወግዶ፡ በእርሱ ቦታ፡ በኦሪታውያኑ አይሁድ ውርስና ቅርስ ላይ ተመሥርቶ፡ ይኸው ዛሬ፡ ሠልጥኖና ተንሠራፍቶ የሠፈነው፡ የኦርቶዶክሳውያኑ ግብፃውያን፡ ሰው-ሠራሽ የምንኵስና ወግ፡ እንዲህ፡ መክበሩና ማስከበሩ፥ መግነኑና መንገሡ ነው።

ለዚህም ማረጋገጫው፡ ዛሬ፡ በምእመናንና በምእመናት ዘንድ፡ ከመመለክ ደረጃ የደረሰው፡ ይኸው ምንኵስና፥ ወይም፡ ጵጵስና፡ "ጳጳስ" ተብሎ፡ ወደኢትዮጵያ የመጣው፡ የኦርቶዶክሳውያኑ ግብፃውያን ተጠሪ፡ ወደኢትዮጵያ ተልኮ፡ በቅኝ ገዢነት ሥልጣኑ፡ መንበሩን፡ ከባለቤቱ ቀምቶ እስከያዘበትና ከዚያ ተያይዘው በቀጠሉት ዘመናት፥ እስከቅርቡ ጊዜ ድረስ፡ በኢትዮጵያ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ የመንፈሳዊው ዘርፍ የኾነው፡ የቤተ ክህነቱ ባለመንበር፡ እርሱም፡ የአኩሱሙ ንቡረ እድና ኋላ "እጨጌ" የሚል የማዕርግ ስም የተሰጠው፡ የኢትዮጵያው ሊቀ ካህናት፡ በቅዱሱ ጋብቻና በክቡሩ ትዳር ተወስኖ የሚኖር፡ ኢትዮጵያዊ ካህን መኾኑ፡ በገሃድ የታወቀበት እውነታ ነው።

ሊቀ ሐዋርያት ቅዱስ ጴጥሮስ፡ እግዚአብሔር፡ ቀድሶ የፈጠረውን ሥጋዊ አካል፡ *"ርኩስ ነው!"* ብሎ በመጸየፉ፡ የእግዚአብሔር ቃል፡ "**ዘእግዚአብሔር አንጽሓ፡ አንተ ኢታስተራኵስ!**" ማለትም፡ "**እግዚአብሔር፡ በቅድስና አንጽቶ የፈጠረውን፡ አንተ፡ አታርክሰው!**" ብሎ፡ ሦስት ጊዜያት እንደገሠፀው ኹሉ፡ እግዚአብሔር የሠራውን፡ የጋብቻን ሥርዓት የሚያረክስ፥ የሰው የኾነውን ምንኩስናን ግን የሚቀድስ፡ ይህ፡ የግብፃውያን ፀረ እግዚአብሔርና ፀረ ኢትዮጵያ የኾነው፡ ክፉ ወግ፡ እውነተኞቹን ቤተ ሕዝብ፥ ቤተ ምልክናና ቤተ ክህነት፡ በተዋሕዶ አንድ አድርጋ፡ ዘለዓለማዊዉን መልካም ህልውናዋን በማካኼድ ላይ በምትገኘው፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ዘንድ፡ ቀድሞም አልኖረም፤ ዛሬም የለም፤ ወደፊትም፡ ሊኖር አይችልም። (የሐዋ. ፲፥ ፲፭-፲፮።)

በአንድ ወገን፡ ሥርዓተ ጋብቻውና የትዳሩ ኑሮ፥ በሌላውም ወገን፡ የብሕትውናውና የድንግልናው አኗኗር፡ ኹለቱም ሥርዓቶች፡ ከላይ እንደተጠቀሰው፡ እንደእግዚአብሔር ቃልና እንደመለኮታዊው መመሪያ፡ ተገቢ ሥፍራቸውንና ይዞታቸውን፥ ተፈጻሚነታቸውንና ፍሬያማነታቸውን እንደያዙ፡ እስከዛሬ ኖረዋል፤ ለወደፊቱም፡ በዘለዓለማዊነት ህልውናቸው ይቀጥላሉ።

ባሕታዊውና ድንግላዊው ቅዱስ ጳውሎስ እንኳ፡ አረማውያንና አሕዛብ ተከታዮቹ ለነበሩት፡ ለአዲሶቹ የክርስትና አማኞቹ በጻፋቸው መልእክቶቹ ውስጥ፡ በዚህ ረገድ: ለእነርሱ የሰጣቸው ቋሚ መመሪያ፡ ይህንኑ ጥንታዊዉንና አማናዊውን የቅዱሱን ኪዳን ኢትዮጵያዊ ሥርዓት መሠረት በማድረግና በማጽናት መኾኑን፡ ከዚህ የሚከተሉት፡ የቅዱሳት መጻሕፍት ጥቅሶች፡ አረጋግጠው ይመሰክራሉ።

ሀ . "እሙን ነገር፡ ዘይፈቅድ ይሠየም ጳጳሰ፡ ሠናየ ግብረ ፈተወ። ወባሕቱ ርቱዕ ይሠየም ጳጳሰ፤ ዘኢያደሉ ለገጽ፥ ዘአልቦ ምክንያት፥ <u>ዘአሐተ ብእሲተ አውሰበ፤</u> ብእሲ፡ ንቁህ ወጠቢብ፥ ወመፍቀሬ ነግድ፥ ዘአንጽሐ ርእሶ፥ መምህር ወመገሥጽ፤ ዘኢያበዝኅ ሰትየ ወይን፥ ዘኢያፈጥን እዴሁ ለዘቢጥ፥ ባቍዕ፥ ዘኢይትገአዝ፤ ዘኢያፈቅር ንዋየ፤ <u>ዘሠናይ ሥርዓተ ቤቱ፥ ዘቦ ውሉድ፡ ዘይትኤዘዙ በኵሉ ንጽሕ፤ ወዘሰ ኢይክል፡ ሠሪዐ ቤቱ፡ እፎኑ ያስተሓምም ቤተ እግዚአብሔር።"</u>

ማለትም፡ "'ጵጵስናን ሊሾም የሚወድድ ቢኖር፡ መልካም ሥራን ተመኘ!' የሚለው ቃል፡ የታመነ ነገር ነው። ነገር ግን፡ ጳጳስ ኾኖ ሊሾም የሚገባው፡ ፊት አይቶ የማያደላ፥ ምክንያት የሌለበት፥ <u>የአንዲት ሚስት ባል፥</u> ንቁ ሰው፥ ብልህ፥ እንግዳ ተቀባይ፥ ራሱን፡ በንጽሕና የጠበቀ፥ የሚመክር፥ የሚያስተምር፥ የማይሰክር፥ ለመማታት የማይፋጠን፥ በምክሩ የሚጠቅም፥ የማይጣላ፥ ገንዘብ የማይወድድ፥ <u>ቤተሰቡን፡ በመልካም የሚያስተዳድር፥ በፍጹም ንጽሕና የሚታዘዙ ልጆች ያሉት፤ ቤቱን በሥርዓት መያዝና መምራት የማይችል ሰው፡ የእግዚአብሔርን ቤት፡ እንደምን ያስተዳድራል?"</u> (፩ጢሞ. ፫፥ ፩-፭።)

ለ . <u>"ብእሴ፡ ዘአሐተ ብእሲተ አውሰበ፥</u> ኄሩየ፥ ዘኢየሓምይዎ በእኩይ፥ <u>ዘቦ ውሉድ ማሃይምናን፡ ዘኢያስተዋድይዎሙ በምርዓት፡ እለ ኢኮኑ ዝሉፋነ እለ ይቴዘዙ፡</u> ወርቱዕ ይሠየም ጳጳስ።"

ማለትም፡ "ጳጳስ ኾኖ ሊሾም የሚገባው፡ <u>የአንዲት ሚስት ባል የኾነ፥</u> የተመረጠ፥ በክፉ ነገር የማያሙት፥ <u>በዝሙት ያልተከሰሱና ያልተነቀፉ፥ የሚታዘዙና የታመኑ ልጆች ያሉት ይኹን!"</u> (ቲቶ ፩፤ ፮-፯።)

ለመኾኑ፡ ለዚህ ሥርዓት ተፃራሪ በኾነው፡ በግብፃውያኑ ሰው-ሠራሽ ወግ፡ እስካኹንና ዛሬም፡ ለጵጵስና ማዕርግ ከበቁትና የኢትዮጵያ ገዳማት ካፈሯቸው መነኮሳት መካከል፡ በቅዱሱ ጋብቻና በክቡሩ ትዳር፥ በልጆች አስተዳደጉና በቤተሰብ አስተዳዳሪነቱ በኵል ያለው መሥፈርት ቀርቶ፡ ሌሎቹን፡ የሓዋርያውን መሥፈሪያዎች፡ አንዳቸውን እንኳ፡ አሟልተው የተገኙ፡ የትኞቹ ናቸው?

ለዚህ ጥያቄ፡ ተገቢና ትክክለኛ የኾነውን መልስ፡ በምስክርነት ቃላቸው፡ ለመንፈስ ቅዱስና ለየኅሊናቸው፥ ለኪዳናውያንና ለኪዳናውያት ወገኖቻቸውም ይሰጡ ዘንድ፡ ከእርስዎና እርስዎን ከመሰሉ ደጋፊዎቻቸው በስተቀር፡ እውነተኞች፡ የእግዚአብሔር አማኞች ለኾኑ፡ ኢትዮጵያዊ እና ኢትዮጵያዊት ትተነዋል።

፫ኛ፡ እርስዎ፡ እንኳንስ ከመንፈሳዊው የእውቀት ብቅዓት ደረጃ ቀርቶ፡ ከነፍሳዊው እንኳ፡ ገና ያልተቃረቡ፥ ለሥጋዊዉም እንኳ ቢኾን፡ ከእንጭጭነቱ ዓቅም እንኳ ያልደረሱ ስለመኾንዎ፡ ራስዎን ያጋለጡበትን አጻጻፍዎን፡ እንደገና፡ አተኵረው ይመልከቱት! ይኸውም፡ *"እኔ እኮ የሚገርመኝ ማህበረ ቅዱሳን እና የሚመለከታቸው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ አካላት ለምን እንደዚህ አይነት አካላትን በዝምታ እንደሚመለከታቸው ነው !!!"* ብለው የጻፉት ቃል ነው።

የእርስዎ አንሦ፡ እነዚህ የሰዎች ድርጅቶች፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ላይ ዳኝነት እንዲሰጡና እንዲፈርዱ ጠየቁ አይደለም?

መልካም! ለዚህ አባባልዎና አጻጻፍዎ፡ በእውነተኛ ንስሓ እስካልተመለሱ ድረስ፡ የሚጠብቅዎ ምን እንደኾነ፡ የተገነዘቡት አይመስልም። ይህን ነገር በሚመለከት፡ መለኮታዊው ቃል የሰጠው፡ የመጨረሻ ብያኔ፡ ይኸውልዎ! በማስተዋልና በጥንቃቄ ያዳምጡት!

"በእንተዝ፡ እብለክሙ! ኵሉ ኃጢአት፥ ወፅርፈት፥ ይትኀደግ ለሰብእ፤ ወዘሰ ፀረፈ፡ ላዕለ መንፈስ ቅዱስ፡ ኢይትኀደግ ሎቱ። ወዘሰ ነበበ፡ ቃለ፡ ላዕለ ወልደ እጓለእመሕያው፡ ይትኀደግ ሎቱ፤ ወዘሰ ነበበ፡ ላዕለ መንፈስ ቅዱስ፡ ኢይትኀደግ ሎቱ፡ ኢ፡ በዝ ዓለም፤ ወኢ፡ በዘይመጽእ።"

ማለትም፡ "ስለዚህ እላችኋለሁ፤ ለሰው፡ ኃጢአትና ስድብ ኹሉ ይሰረያል፤ መንፈስ ቅዱስን የሰደበ ግን፡ አይሰረይለትም። በማርያም ልጅ ላይ፡ ቃልን የተናገረ ይሰረይለታል፤ በመንፈስ ቅዱስ ላይ የተናገረ ግን፡ በዚህ ዓለምም ቢኾን፡ በሚመጣውም ዓለም ቢኾን፡ አይሰረይለትም።"

------------------------------------